


# የሲይትል አየር ማረፊያ ዘላቂ አየር ማረፊያ ዋና እቅድ (SAMP)

## የክልላችንን እድገት ለማስተናገድ እቅድ ማውጣት

የፒዩጀት ሳውንድ ክልል በ 2035 በተጨማሪ አንድ ሚሊዮን የህዝብ ቁጥር ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል። የዘላቂው የኣይሮፕላን ማረፊያ ዋና እቅድ (SAMP) ለሲያትል-ታኮማ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ (SEA) ልማት ንድፍ ሆኖ ያገለግላል፣ ይህም የወደፊት ዕድገት; ፍላጎትን ለማሟላት ስልታዊ የሆነ ንድፍ ወደ ልማት ይመራል።

**SAVE THE DATE: OCTOBER 21**

ንድፍ NEPA EA በኦክቶበር 21፣ 2024 ይታተማል፣ የሕዝብ አስተያየት ጊዜ ዲሴምበር 5፣ 2024 ያበቃል። በSAMP ላይ ወቅታዊ መረጃ ያግኙ እና እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ይወቁ፡

**sampntpenvironmentalreview.org**

በተጨማሪ፣ ለወደፊት የተተነበየውን ግምት ውስጥ በማስገባት የተሳፋሪ እና የጭነት ፍላጎትን ከማጤን SAMP የወቅቱን መገልገያዎችን፣ መሠረተ ልማቶችን እና ስራዎችን ይመረምራል— ወደፊት አምስት፣ 10 እና 20 ዓመታትን በማየት ሁኔታዎችን ይመለከታል። የዕቅድ ሥራው የተከናወነው ከወደቡ ዘላቂነት እና የኃይል ውጤታማነት ግቦች ጋር ለማጣጣም ነው፤ ምን እንደሚገነባ፤ እንዴት እንደሚገነባ እና እንዴት ሥራ ላይ እንደሚውል ይገልጻል፤ ይህ ሁሉ በሲያትል የኣውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ዘላቂ አፈፃፀምን  ለመደገፍ ነው።

ሲይትል ኣይሮፕላን ማረፊያ በቁጥር (2023):

- 50.8 ሚሊዮን መንገደኞች
- 35 አየር መንገድ
- 93 የማያቋርጥ የሀገር ውስጥ እና 30 ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች
- በSkytrax's (የዓለም አየር መንገድ ሽልማቶች) ከ100 ለአሜሪካ አየር ማረፊያዎች ውስጥ ለ3 ዓመታት በተከታታይ ከፍተኛውን ደረጃ አግኝቷል

## SEA SAMP በቅርብ ጊዜ የታቀደ ሥራ/ ውጥን ሁኔታዎች ግምገማ

የሲይትል አየር ማረፊያ ዘላቂ  ዋና እቅድ (SAMP) እ.ኤ.አ. በ2018 ተጠናቅቋል። ከSAMP፣ ወደቡ 31 የአቅራቢያ ውጥኖችን (NTPs) ለይቷል እና የአካባቢ ግምገማ (2018) የማጠቃለያ ሂደቱን አጠናቅቋል። በአሁኑ ጊዜ የብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ቋሚ መመሪያ (NEPA) የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ እየተካሄደ ነው፤ ረቂቅ NEPA ሰነድ በኦክቶብር 21, 2024 ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል። የ NEPA ሂደቱ እንደተጠናቀቀ, የግዛቱ የአካባቢ ጥበቃ ቋሚ መመሪያ (SEPA) ግምገማም ይከተላል።

SAMP የታዘዘው 31 NTPs ውጤታማነትን, ደህንነትን, ወደ አውሮፕላን ማረፊያ መዳረሻ, እና ለአየር መንገዶች እና ለአውሮፕላን ማረፊያ ድጋፍ ተቋማትን ያሻሽላል. NTPs, ከተፈቀደ፤ በ 2032 ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል፤ ወይም በግንባታ ላይ ይሆናል።

NTPs የሚከተሉትን ያካትታል፤

- 19 ተጨማሪ በሮች ያለው ሁለተኛ ተርሚናል
- ከፍ ያለ የአውቶቡስ መንገድ፤ የመኪና መከራያ ተቋም፣ አዲሱን ተርሚናል እና ዋና ተርሚናልን የሚያገናኙ ጣቢያዎች ይኖሩታል
- የአየር ጭነት እድገትን ለማስተናገድ የሚይስችል የዕቃ መጫኛ መገልገያዎች
- የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶችን ማደስ
- የአየር ማረፊያ ማሻሻያዎች የደህንነት እና ውጤታማነት ለማሻሻል
- አዲስ የመኪና ማቆሚያ መሠረተ ልማት
- ለዘላቂ የሆነ የአውሮፕላን ነዳጅ ተጨማሪ ተቋማት

የአካባቢ ግምገማ ማለት የአንድ ፕሮጀክት/ ውጥን ምን ዓይነት ተፅዕኖዎች በአካባቢ ላይ ሊያስከትል እንደየሚችል የመገምገም ሂደት ነው። NEPA የፌደራል ድርጅቶች አንድ ድርጊት በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት እንዲገመግሙና፤ የሕዝብ አስተያየት እንዲሰጡትም እድል እንዲያገኙም ይጠይቃል። አንድ የአካባቢ ግምገማ (EA) የፌዴራል እርምጃ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረው እንደሆን ለመወሰን ዝግጁ ነው፤ ወይ የሚለውን ለመወሰን የአካባቢ ግምገማ (EA) ተዘጋጅቷል። የትኛውም እርምጃ በከፊል ያልተካተተ እና የአካባቢ ተጽዕኖ መግለጫ (EIS) የማይፈልግ፣ እርግጠኛ ያልሆኑ ተፅዕኖዎች ያለው፣ ወይም ያልተፈቱ የአካባቢ ጉዳዮች ያለው፣ የEA ዝግጅት ያስፈልገዋል።

# የአካባቢ ጥናት የጊዜ ሰሌዳ

2018
2019
2020
2021
2022
2023
2024
2025
2026

የበልግ 2018: ፍጻሜ/ክንውን

መጀመሪያ 2019 - የበጋ 2024: የ SAMP NEPA EA ሰነዶች እና ትንተናዎች ልማት

በልግ 2024፡ : NEPA

- ሴፕቴምበር 20፡ የNEPA የ30 ቀን ረቂቅ ጽሑፍ ማስታወቂያ ይለቃል
- አክቶበር 21፡ NEPA EA ሰነዶች ይለቀቃል
- አክቶበር 21 - የወኪል ድርጅት እና የህዝብ አስተያየት ክፍለ ጊዜ

ጸደይ 2025: NEPA EA የመጨረሻ ሰነድ እና ውሳኔ

በጋ 2025 - በልግ 2025 (በQ2 2025 መጨረሻ)፡
: የ SEPA ወኪል ድርጅት እና የህዝብ አስተያየት ክፍለ ጊዜ

በ2025 መጨረሻ (Q4 2025): SEPA የመጨረሻ ሰነድ እና ውሳኔ

# የሕዝብ ተሳትፎ

ወደቡ ህዝብ በቀላሉ ሊደረስበት እንዲሁም ለመረዳት የሚቻልበት፤ አስተያየት በመስጠት በሚይስችል ሂደት ላይ የተቆረቆረ ነው። የ45-ቀን የህዝብ አስተያየት ጊዜ ኦክቶበር 21፣ 2024 ከጀመረ በኋላ የህብረተሰቡ አባላት በስድስት ቋንቋዎች የተተረጎሙ መረጃዎችን መከለስ እና በአስተያየቱ ጊዜ ውስጥ አስተያየቶችን በህዝባዊ ስብሰባ፣ በመስመር ላይ፣ በኢሜል ወይም በመደበኛ ፖስታ ማቅረብ ይችላሉ። ሰነዱ በድረ-ገጻችን ላይ እና በቡሪይን፤ ዲሞይንስ እና ሲታክ ውስጥ ባሉ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍትቶች ውስጥ ይገኛል።

# የሕዝብ ስብሰባዎች

## ለሕዝባዊ ስብሰባዎቻችን ቀኑን ይመዝግቡት

የህዝብ አስተያየት ለመስጠት በህዝባዊ ስብሰባዎቻችን ላይ ይቀላቀሉን፡-:

- ህዝባዊ ስብሰባዎች በቡይሪይን፤ ሲታክ እና ዲሞይንስ ውስጥ ይካሄዳሉ
- የህዝብ ስብሰባ ቀኖችም ኑቨምበር 13 እና 14 ይሆናል
- ወደ ልዩ ቦታዎች እና ጊዜዎች ይምጡ

የህዝብ አስተያየት በኦክቶበር 21 ከተከፈተ በኋላ ይፋዊ ለሆኑ አስተያየቶች ከሶስቱ ህዝባዊ ስብሰባዎች ውስጥ በአካል በመገኘት፤ በኢሜል፣ በፖስታ ወይም በSAMP ድህረ ገጽ ላይ ሐሳብዎን ሊያቀርቡ ይችላሉ።
የቅርብ ጊዜውን መረጃ ለማግኘት ድረ ገጻችንን ይመልከቱ።
: https://www.sampntpenvironmentalreview.org/

Port of Seattle®
www.portseattle.org

ስለ ወደብ እና የሲይትል አውሮፕላን ማረፊያ መረጃ እንዲደርስዎት ተመዝግበው ደንበኛ ይሁኑ፤
https://subscribe.portseattle.org/publications